Press Release

Embassy of the United States of America
Addis Ababa, Ethiopia
2014/45

For further information, call 011-130-7033
http://ethiopia.usembassy.gov

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ውስጥ የተመሰረተውን የመሬት ምርምርና ልማት ትስስር (ኔትዎርክ) በይፋ መከፈቱን አበሰረ

የምርምር ትስስሩ በኢትዮጵያ በመሬት ጉዳዮች ዙሪያ የሚደረጉ የምርምር ሥራዎች ለብሔራዊ ልማት በሚውሉበት አቅጣጫ ላይ የሚያተኩር ይሆናል

ህዳር 16፣2007 ዓ.ም.፤ባህር ዳር፡- የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ተጠባባቂ ዳይሬክተር ጌሪ ሊንደን፤ የባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ፣የመሬት አስተዳዳር ተመራማሪዎችና ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የመሬት ምርምርና ልማት ትስስር ምረቃ ላይ ለመገኘት የመጡ ምሁራን በተገኙበት በመሬት ምርምር ዙሪያ ያሉትን ክፍተቶች ይሞላል የተባለለትን ትስስር መርቀው ከፍተዋል፡፡

የመሬት ልማት ለሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ያለው ሚና ወሳኝ ቢሆንም በሀገር አቀፍ ደረጃ በቂ የሆነ የመስክ መረጃ በመሰብሰብ በዘርፉ በመረጃ ላይ የተመሠረተና ለልማት የሚበጅ ፖሊሲ መቅረጽ የሚቻልበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ አዲሱ ትስስር በመሬት ዙሪያ የሚደረጉ ምርምሮች ለውይይትና ለክርክር የሚቀርቡበትና ታትመው የሚሰራጩበትን መድረክ የሚያመቻች ይሆናል፡፡ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ መጪውን ትውልድ መመገብ የተሰኘ ፕሮግራም አካል በሆነው የመሬት መርሀ ግብር በኩል ለዚህ ትስስር ምሥረታ ድጋፍ ያደረገ ሲሆን፤ በሀገሪቱ ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች፣የምርምር ተቋማት፣መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ምርምሮችን በማካሄድ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡

የምርምር ትስስሩ በመሬት ዙሪያ የሚሠሩ ምርምሮችን የሚያስተዋውቅና ውጤቶቹን የሚያሰራጭ ሲሆን በአብዛኛው በመሬት ጉዳይ ዙሪያ ለሚያደርገው እንቅስቃሴ በገጠሩ የሀገሪቱ ክፍል በሚገኘው ሕዝብ ላይ በይበልጥ ያተኩራል፡፡ በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ የሚገኘው ይኸው ትስስር በዘርፉ የሚደረጉ ምርምሮችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች ማከማቻም ይሆናል፡፡

የዚህ ትስስር መሥራች አባላት ከሀገሪቱ ቀዳሚ የትምህርትና ምርምር ተቋማት ከሆኑት የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ፣ የሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ፣የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር፣ የማህበራዊ ጥናት መድረክ፣ የኢትዮጵያ መሬት አስተዳደር ማህበር፣የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የኢፌዲሪ የግብርና ሚኒስቴር እና የኢፌዲሪ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ናቸው፡፡

ትስስሩ በዘርፉ ያሉ ሀገር በቀል የሆኑም ሆነ የውጭ ተቋማትን፣ማህበራትንና ሌሎች የትስስር ማዕከላትን በአባልነት ለመቀበል ዝግጁ ነው፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ተጠባባቂ ዳይሬክተር ጌሪ ሊንደን የትስስር መረቡ የመሬት አስተዳደርን በማሳለጥ ረገድ ስለሚኖረው ጠቀሜታ ሲናገሩ፡- “የዚህ ትስስር ስኬት መለኪያ የሚሆነው በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ላይ ከተቀመጡ ግቦች ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ ለመሬት ልማት የፖሊሲ ቀረጻ የምርምሮቻችሁ ውጤቶች አጋዥ ሲሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ሁላችሁም ይህንን ዕድል በመጠቀም የዚህን ታላቅ ሀገር ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ሰላማዊ ህዳሴ በማረጋገጥ በብቃት ላይ የተመሠረተ፣ዘላቂነት ያለውና ትክክለኛ የሆነ የዚህ ሰፊ የሆነ የሀገሪቱን የመሬት ሀብት አስተዳደር እውን እንድታደርጉ ጥሪዬን አቀርባለሁ” ብለዋል፡፡

###